# የታለች?

የሀገርነት ዕድሏ፥
ዕጣዋ ቢጨንቃቸው
የማንነቷ መጎሳቆል፥
መሸርሸሩ ቢያውካቸው
የትውልዱ ትልም ጉዞ፥
አቅጣጫው ቢረብሻቸው
በመስዋዕትነት ያፀኑት፥
አንድነቷ ቢቆጫቸው
ቀና ብለው አዩዋት . . .
ከተንጋለሉበት
ተፋልመው ከሞቱበት
ተዋግተው ከተሰዉበት
አስከብረዋት ከወደቁበት።
ቀና ብለው አዩዋት . . .
*«እውነት እሷ ናት?*
*ያቺ የወደቅንላት*
*ሳናመነታ የሞትንላት*
*ሕይወት ያበረከትንላት*
*ደምና አጥንት የገበርንላት*
*ከልጅ፥ ከሚስት፥ ከእናት፥ ከአባት*
*አብልጠን የሳሳንላት*
*ስሟ የሚርበን የሚጠማን፥*
*አፈሯን የቃምንላት*
*እውነት እሷ ናት?»* . . .
ቀና ብለው አዩዋት
ሊያዝኑላት ይሁን ሊያዝኑባት
ሊያለቅሱላት ይሁን ሊያለቅሱባት
ሊፈትኗት ይሁን ሊታዘቧት
ሊያማክሯት ይሁን ሊሞግቷት
ባያውቁትም . . .
ቀና ብለው አዩዋት
አስተዋሏት . . .
የፈራረሰው ስጋቸው
የተከሰከሰ አጥንታቸው
ቢቀሰቅሳቸው
እረፍት ቢነሳቸው
ጠላትን የሚወጋው፥
አልተኛምና ዐፅማቸው
ከትቢያዋ ቢዋሃዱም፥
አልሞተምና መንፈሣቸው
ሕያው ነውና ወኔያቸው
ቀና ብለው አዩዋት . . .
*«እውነት እሷ ናት?*
*ያቺ የሞትንላት*
*ተሰዉተን ያስከበርናት*

*እሷ ናት?*
*ምነው ገጿ ተለወጠ?*
*ዳር ድንበሯ ተናወጠ*
*ምነው መልኳ ተበላሸ?*
*ሰንደቅ ክብሯስ ተንቋሸሸ*
*ምነው ሕዝቧስ ተለያየ?*
*በዘር በጎጥ ተከለለ»*
እያሉ . . . ቀና ብለው አዩዋት
ይህ የዘመን እኩይ፥
ማንነቷን ሲያጎድፍባት
ሙሉነቷን ሲያጎድልባት
አዩዋት . . .
እንምራሽ ያሏት ልጆቿ፥
በማናለብኝነት ታውረው
በጥቅም ተደልለው
በክህደት ተሞልተው
መሠረታቸውን ረስተው
ክብሯን እንደሸቀጥ ቸርችረው
በየዓለማቱ ከተሞች ለ«ድርድር» አቅርበው . . .
በ«አግሪቢዝነስ» ድራማ
ስትሸነሽን ስትደማ
ለም መሬቷ ሲቸረቸር
ለ«ፎሪን ከረንሲ» ለቀማ
የበዩ ተመልካች ልጆቿ
ለምድራቸው ባእድ ሆነው
በዘመናዊ ባርነት
ለውጭ ነጋዴ ተሸጠው
ኢትዮጵያ ስታነባ
የሀፍረት ሸማ ተከናንባ
አዩዋት . . .
በፀፀት እሳት ሊነዱ
ሁለተኛ ሞት ሊሞቱ!
አዩዋት . . .
*«እውነት እሷ ናት?*
*የሞትንላት*
*ያከበርናት*
*ያስከበርናት*
*እውነት እሷ ናት?»*

(በ*ማርች* ወር 2006 ነበር **«የታለች?»** *ለመጀመሪያ* ጊዜ የተጻፈችው . . . የኢትዮጵያ የባሕር በር ጉዳይ ኢትዮጵያውያንን በድጋሚ አንገታችንን ባስደፋን ሰሞን። ዛሬ ደግሞ የኢትዮጵያ የእርሻ መሬት ለውጭ መንግሥታትና ባለሀብቶች እየተቸረቸረ ባለበት ወቅት እነሆ **«መሬት ላራሹ! . . .መሬት የለሹ»**ን በጩኸቷ ለማገዝ ብቅ ብላለች . . . ጥቂት ስንኞችን ጨምራ።)

---

**ቴዎድሮስ አበበ**
Springfield, VA
ታኅሣስ ፰ ቀን ፳፻፪ ዓመተ ምሕረት | December 17, 2009